**ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ታህሳስ 4 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**በሕዝቡ ላይ እየደረሰ ያለው ወከባ ተባብሶ ቀጥሏል፤ 400 አርሶ አደሮች ሸዋሮቢት እስር ቤት ታጐሩ፤ በጅማ ዩኒቨርስቲ ከፍተኛ ብጥብጥ ተከሰተ፣ በመቀሌ ሁለት ተማሪዎች ክፉኛ ቆሰሉ፣ በጅጅጋ 15 ተማሪዎች ታሰሩ፤ መለስ ዜናዊ ባለሥልጣናቱን አግልሎ ላልተወሰነ ጊዜ ከስራ አገዳቸው፤ በድብቅ 2 ብርጌድ የፌዴራል ፖሊስ አስመረቀ ..................**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ለማንበብ እዚህ ይጫኑ ............**

በረሀ ወለዱ ወያኔ በሕዝቦች ላይ የሚያደርሰው በደልና ግፍ ከቀን ወደቀን እየከፋና እየሰፋ መምጣቱን ከተለያዩ አካባቢ የሚደርሱን ዘገባዎች ገለፁ::

እንደደረሰን ዘገባ ከሆነ በወሎ ክፍለ ሀገር በከሚሴ፣ በባቲና በሰንበቴ የአካባቢው ነዋሪዎች ላይ የወያኔ ቡድን ከፍተኛ እንግልትና ስቃይ እያደረሰባቸው በመሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ከፍተኛ ምሬት እያሰሙ የአለም ሕብረተሰብ እንዲያውቅልን ሲሉም ጥሪ ማስተላለፋቸው ታውቋል::

ከአንድ ሳምንት በፊት በዚህ በከሚሴ፣ በባቲና በሰንበቴ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችን የወያኔ ቅልብ ወታደሮች «የኦነግ ደጋፊ፣ ናችሁ የኦነግ ታጣቂ ኃይልን መንገድ ትመራላችሁ» በማለት ሕፃን አዋቂ ሳይል ሕዝቡን ሰብስበው በዱላ ከደበደቡ በኋላ ይህም አልበቃ ብሏቸው መልሰው ከ3ቱም ወረዳዎች ከ700 በላይ አባወራዎችንና ወጣቶችን አፍሰው ለእስር የዳረጓቸው መሆኑን የለገፀው ይኸው የደረሰን ዘገባ 300 ያህል የሚሆኑትን አባዎራዎች በየወረዳዎቹ ፖሊስ ጣቢያ ያሰሯቸው ሲሆን፣ የተቀሩትን 400 ወጣቶችን ደግሞ ሸዋ ሮቢት እስር ቤት እንዳጐሯቸው ለማወቅ ተችሏል::

ዙሪያውን ተወጥሮ ያለው ወያኔ የሚደርስበትን ጫና ለማስተንፈስ ሲል ብቻ ያለምንም በቂ ማስረጃ ያለአንዳች ርህራሄ በዜጐች ላይ ይህን መሰል ግፍ እየፈፀመ ከመሆኑም ባሻገር አመታዊ ግብር እየጨመረ የማዳበሪያ እዳ ባልታሰበ ሰዓት እንዲከፍሉ እያስገደደ በዚህም አቅም የሌለውን የራሱ ደጋፊ ለማድረግ ጥረት ቢያደርግም አልሳካ ያለው የወያኔ በድን ኦሮሞ አካባቢ ሲደርስ « ኦነግ ነህ» አማራ ክልል ሲደርስም እንደዚሁ ሌላ ታፔላ እየለጠፈ በማዋከብ በሕዝብ ላይ እየጫወተ መሆኑንም ይኸው ዘገባ ገልጿል::

ከዚህም ቀደም ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባሎች እና ደጋፊዎች ናችሁ በሚል ብቻ በብዙ ቦታዎች የሀገሪቱን ዜጐች እንደሳር በጥይት እያጨደ ያለው ወያኔ ካለፈው ስህተቱ ከመማር ይልቅ የጥፋቱን አካሄድ በማሻሻል ግልፅ በሆነ መንገድ በዜጐች ላይ የጥፋት በትሩን እያሳረፈ መጥቶ ዜጐችን ያለአንዳች ጥፋታቸው ከየቤታቸው እያፈሰ ማስመሰያ ታፔላ እየለጠፈ ለእስር እየዳረጋቸው መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቶ አሁንም በከሚሴና አካባቢዋ በሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ላይ እየወሰደ ያለው አስከፊ እርምጃ በእጅጉ አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ ሰቅጣጭ ርህራሄ የለሽ መሆኑንም ጨምሮ ገልጿል::

በቦረና፣ በጐንደር፣ በሐረር፣ በትግራይ እና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ ተቃዋሚዎችን ትረዳላችሁ በሚል ሰበብ በርካታ ሺህ የሀገሪቱን ዜጐች ወያኔ በቅልብ ጦሩ እያንገላታና እያዋከበ አልፎ ተርፎም ለእስር እየዳረገ በአንድ እስር ቤት ከ6ሺህ በላይ ዜጐች

እንዲታጐሩ አድርጐ ለጠኔ እና ለበሽታ እየዳረጋቸው መሆኑን የገለፀው ዘገባ በተለይ በአማራ ተወላጆች ላይና በኦሮሞ ተወላጆችም ላይ የሚወስደው ዘግናኝ እርምጃ ወደር የለሽ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አስረድቷል፡፡

የተማረ ኃይል እና በኢኮኖሚ እራሱን የቻለ ማህበረሰብ የሚያስፈራው ወያኔ በተለያዩ ጊዜያት የተማሩ የሀገሪቱን ዜጐች ለማሰር ሲል ብቻ በየመኪናው ላይ ቦምብ እየጣለና ፈንጅ እያጠመደ በርካታ ንፁኃን ዜጐች ለህልፈት ከመዳረጉም በላይ በምንም መልኩ ከፍንዳታው ጋር ሊገናኙ የማይችሉ ነገር ግን የአይናቸው ቀለም አለማረኝም የሚላቸውን ሁሉ እየሰበሰበ ለእስር የዳረጋቸው ሲሆን፣ ከ5 ዓመትና ከዚያም በላይ ያለአንዳች ጠያቂና ፍ/ቤት ቀጠሮ በድብቅ እስር ቤቶች ታጉረው የሚገኙ በርካታ የሀገሪቱ ምሁራኖች እንዳሉ ይኸው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

ዛሬ ወያኔ በጣለብን ማዕቀብና ባመጣብን ጣጣ የተነሳ የዕለት ጉርስ ለማግኘት ላይ ታች እየባዘንን ባለንበት ወቅት ይህም አልበቃ ብሎ በተቃዋሚ ፖርቲ አባልነት ዜጐችን እየፈረጀ ለእንግልትና ለስደት መዳረጋችን በጣም የሚያሳዝን ቢሆንም ይህንን ሽክም ይዘን የት ድረስ እንደምንጓዝና እና እስከመቼ እንደምንቆይ አይገባኝም ሲሉ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር በቁጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል ሲል ዘገባው አብራርቷል፡፡

የህዝቦች ደም ቀለቡ የሆነው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ደግሞ ተማሪዎችን እርስ በእርስ እያጋጨ መሆኑን ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የሚወጡ ዘገባዎች አጋለጡ፡፡

በመቀሌ፣ በጅማ፣ በጅጅጋ፣ በጐንደርና በሌሎችም ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን ሰሞኑን የወያኔ ካድሬ አስተዳደር ሰራተኞች የአሜሪካ መንግስት በወያኔ ላይ ያወጣውን ኤች አር 2003 ሕግ እንዳይፀድቅ ለማድረግ እንዲቃወሙ የተማሪዎቹ የነቃ ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ ተነግሯቸው ፊርማቸውን እንዲያኖሩ ቢጠየቁም እምቢ በማለት ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ ጥቂት ተማሪዎች ግን በገንዘብ ኃይልና ቤተሰቦቻቸው የወያኔ ካድሬ የሆኑትን ማስፈረማቸውን ዘገባው ገልጿል፡፡

በተለይም በጅማ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የዩኒቨርስቲው ካድሬ አስተዳደሮች ለተማሪዎቹ ሁለት ጥያቄ አንስተው ድጋፍ እንዲያደርጉ የጠየቋቸው ቢሆንም «እኛአይመለከተንም፣ ለትምህርት ነው የመጣነው፣ የፖለቲካ ሰዎችም አይደለንም» በማለት ምላሽ በመስጠታቸው የወያኔ ደጋፊ የሆኑ ጥቂት ተማሪዎች ብጥብጥ እንዲያነሱ ተደርጐ ግጭት እንደተቀሰቀሰ ከአካባቢው ሾልኮ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

«ኤች አር 2003 ሕግ እንዳይፀድቅ ተቃውሞ አሰሙ፣ በአካባቢው የሚንቀሳቀሱትን ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይሎች አውግዙ» በማለት ለጊዜው ስሙ ያልተገለፀው የጅማ ዩኒቨርስቲ ዲን ለተማሪዎቹ ተማፅኖ ቢያቀርብም ተማሪዎቹ በእምቢታ አቋማቸውን በመግለፃቸው የተደናገጠውና የተናደደው ይኸው ግለሰብ የወያኔ ደጋፊ ናቸው የተባሉ ቁጥራቸው ከ50 የሚይበልጡ ተማሪዎች ፀብ እንዲያነሱ አድርጐ ብጥብጥ እንዲነሳ ከማድረጉም ባሻገር ተወርዋሪ ኃይል ገብቶ በርካታ

ተማሪዎችን አፍሶ ወዳልታወቀ ስፍራ እንዲወስዳቸው ትዕዛዝ መስጠቱና ተግባራዊ መደረጉን ይኸው ሾልኮ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

በተመሳሳይ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ኤች አር 2003 ሕግ ለኢትዮጲያ የማይጠቅም ነገር ግን የኢትዮጵያ ጠላቶች ሀሳብ በመሆኑ የተቃውሞ ድምፅ አሰሙ በማለት በዩኒቨርስው አስተዳደር በኩል መመሪያ ቢተላለፍላቸውም ተማሪዎቹ ለትምህርት እንደመጡና ይህም ጉዳይ እንደማይመለከታቸው ይልቁንም ህጉ ቢፀድቅ ግልፅነትና ተጠያቂነት በኢትዮጵያ ውስጥ ሊሰፍን ስለሚችል ጥሩ እንደሆነ በመግለፃቸው ይህንን ሀሳብ የሚያራምዱ ናቸው የተባሉ ከ270 በላይ ተማሪዎች ለሁለት ቀናት ለእስር የተዳረጉ ከመሆኑም በላይ ይህንን ተቃውሞ ያስተባብራሉ የተባሉ ሁለት ተማሪዎች ደግሞ ማለትም ገበየሁ ጋዲሳ እና ከበደ የተባሉትን ተማሪዎች በዱላ ደብድበው ለከፍተኛ ጉዳት የዳረጓቸው መሆኑን ከአካባቢው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

እነዚሁ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ሁለቱ ተማሪዎች በአካባቢው ምንም ዘመድ የሌላቸው በመሆኑ ወዲያውኑ አፋጣኝ እርዳታ ሊያገኙ ካለመቻላቸውም ባሻገር የደረሰባቸው ድብደባ ከባድ በመሆኑ የተነሳ ሰው ማናገር አቅቷቸው እንደነበረ የገለፀው የደረሰን ዘገባ ተማሪዎቹ ቢሞቱ እንደገና ሌላ ከፍተኛ ብጥብጥ ሊነሳ ይችላል በሚል ፍርሀት ብቻ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ካድሬ አስተዳደሮች ተማሪዎቹ ሆስፒታል ገብተው እንዲታከሙ ማድረጋቸውንም ይኸው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

በጅጅጋ ዩኒቨርስቲም እንደሌሎቹ ዩኒቨርስቲዎች ሁሉ ጥያቄው ለተማሪዎቹ ቀርቦላቸው የነበረ ቢሆንም ተማሪዎቹ አንቀበልም በማለታቸው የተናደደው የዩኒቨርስቲው ዲን የተቃውሞ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ያስተባበሩ ናቸው ያላቸውን ተማሪዎች ቢሮው ድረስ እየጠራ የማስፈራሪያ ቃል የሰጣቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ተማሪ ታሪኩ ፊጣ፣ ተማሪ ኃይሌ የተባሉትን ጨምሮ 15 የዩኒቨርስቲው ተማሪዎችን ለእስር እንዳደረጋቸው ለማወቅ ተችሏል ሲል ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

ከወያኔው መለስ ዜናዊ በቀጥታ በደብዳቤ ለትምህርት ሚኒስትር ለሆነው ለብአዴኑ ታጋይ ዶ/ር ስንታየሁ ለተባለው ግለሰብ የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎች ኤች አር 2003ን እንዲያወግዙ፣ በአካባቢያቸው የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ኃይሎችን እንዲኮንኑ ይደረግ በሚል በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ስንታየሁም ለየዩኒቨርስቲዎቹ በገለፀው መሠረት አቋም ለማስወሰድ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በተማሪዎቹ አሻፈረኝ ባይነት የነመለስ ሀሳብ ውድቅ መሆኑን የገለፀው የትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ ተማሪዎቹ በወሰዱት የፀና አቋም የተደናገጡት የሚኒስቴሩ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ሌላ ዘዴ ለመቀየስ እየተሯሯጡ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል።

ወያኔ ህዝቡን በኑሮ ውድነት፣ ገበሬውን በመሬት ግብር ጫና በመፍጠር በተቃዋሚ ጉራ በመፈረጅ፣ ተማሪውን የእኛን አቋም ደግፍ በሚል ሰበብ እያንገላታ እድሜውን ለማራዘም ያላሰለሰ

ጥረት እያደረገ ቢሆንም በተለያዩ ጊዜያት ተደጋጋሚ ተቃውሞ እየገጠመው ሲሆን፣ አሁንም በተማሪዎቹ የደረሰው ተቃውሞ እጅግ አስደንጋጭ እንደሆነበትም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከግራ ወደቀኝ ማዕበል እንደመታው ጀልባ እየተወዛወዘ ባለበት በዚህ ወቅት «ፖለቲካውን ያባላሹብኝ ነባር ፖለቲከኞች ናቸው» በሚል ሙሉ በሙሉ ስራውን የተቆጣጠረው መሆኑን የቤተ መንግስት ምንጮች ገለፁ፡፡

ሰሞኑን እነዚሁ ምንጮች እንደገለፁት ከሆነ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በነባር ካድሬዎቹና በከፍተኛ ባለሥልጣናቱ ስራ ከመናደዱ የተነሳ በሀገሪቱ ያለውን ሥራ ጠቅላላ ሙሉ በሙሉ በአማካሪዎቹ በመታገዝ እየሰራ ሲሆን ከፍተኛ ባለሥልጣናቱን ያገለለው እስከመቼ እንደሆነም ለማወቅ እንደልተቻለ ገልፀዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት እየተናፈሰ ያለው አንዱ ወሬ ከተገለሉት ሰዎች መካከል የኢሕአዴግ ፕሮፓጋንዳና የምርጫ አስተባባሪ እንዲሁም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የሕዝብ ግንኙነት አማካሪ ነው የተባለው በረከት ስምኦን ከተገለሉት ባለሥልጣናት መካከል አንዱ እንደሆነ ምንጮቹ ጠቁመው ጥርጣሬውን ሊያጉላው የቻለው ብዙ ጊዜ የሀገሪቱን አጠቃላይ ሁኔታ ለውጭ ሬዲዮ መግለጫ የሚሰጠው ይኸው ግለሰብ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው በተለይ ካለፈው ሳምንት ጀምሮ እየተካሄደ ያለውን በሻዕቢያና በወያኔ መካከል መወነጃጀልን ትንፍሽ ሳይል መቅረቱ ጥርጣሬው ያጉላ መሆኑን ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

በቢሮው ውስጥም እምብዛም የማይታየው አቶ በረከት ስምኦን ለጊዜው ተብለው ከስራቸው ላይ እንዲገለሉ ከተባሉት ባሥልጣናት መካከል አንዱ ሳይሆን አይቀርም በማለት ምንጮቹ ጠቅሰው ቀድሞ የምርጫ ዘመቻውን ሲከታተልና ሲመራ የነበረ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በአሁን ወቅት ወያኔ የማስመሰያ ምርጫ ዘመቻ ላይ እንዳይሳተፍ ታግዶ ሙሉ በሙሉ ሴኩቱሬ ጌታቸው የተባለው የወያኔ ካድሬ እንደተረከበው ምንጮቹ ጠቅሰዋል፡፡

መለስ ይህን እርምጃ የወሰደው በሁሉም አቅጣጫ ስርዓቱ ላይ ኪሳራ ስለደረሰበት መሆኑን ምንጮቹ ጠቅሰው በአሁን ሰዓት ከየትኛውም ፓርቲ ያልወገኑ ነገር ግን በከፍተኛ ገንዘብ ክፍያ ካስቀመጣቸው ስድስት አማካሪዎች ጋር አብሮ እየሰራ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በአሁን ሰዓት መለስን ያማክራሉ የተባሉት የደርግ ሊቀመንበር የነበረውን መንግስቱ ኃይለማርያምን ሲያማክሩ የነበሩት እነ ሽመልስ ማዘንጊያና ሸዋንዳኝ በለጠ የሚገኙበት መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

ደርግን የተሳሳተ እርምጃ እንዲወስድና በርካታ ግፎች እንዲፈፅም ገፋፍተዋል የተባሉት እነዚሁ ሁለት አማካሪ ተብዬ ግለሰቦች አሁንም ለመለስ ዜናዊ አማካሪ ሆነው ከበረሀ ድረስ አብረው የመጡትን የሕወሓትና የብአዴን ታጋዮች አግልሎ ከእነዚህ ሰዎች ጋር እየሰራ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በአሁን ሰዓት ብቻውን ሥልጣኑን ተቆጣጥሮ በአማካሪ ብቻ እየሰራ ያለው የወያኔ መሪ መለስ ምናልባትም ከባለሥልጣናቱ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ሳይጨቃጨቅ እንዳልቀረና በዚህም ምክንያት እራሱን ሊስት እንደቻለ ያላቸውን ግምት ምንጮቹ ሰንዝረዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ማክሰኞ ታህሳስ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድንገት በቢሮው ውስጥ ታምሞ እንደነበርና ህክምናውን የሚከታተሉለት ዶክተሮች ተጠርተው የሕክምና እርዳታ እንዳደረጉለት የቤተ መንግስት ምንጮች ገለፁ::

ማክሰኞ እለት ረፋዱ ላይ አራት የወያኔ ባለሥልጣናት ጋር በቢሮው ውስጥ ለሁለት ሰዓታት ያህል ሲነጋገሩ እንደቆዩ የገለፁት ምንጮች ባለሥልጣናቱ ከቢሮ ከወጡ ጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በተቀመጠበት እራሱን ስቶ እንደነበርና በአስቸኩዋይ ሀኪሞቹ ተጠርተው የሕክምና እርዳታ እንዳደረጉለት ለማወቅ ተችሏል ሲሉ ምንጮቹ ገልፀዋል::

ወያኔ ባደረበት ስጋት የተነሳ በየጊዜው ያለበትን ፍርሀት ለማስወገድ በማሰብ ብቻ በተለያዩ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ለ6 ወር እና ከዚያም በታች እያሰለጠነ ብዙ ሺህ ጦር ያስመረቀ ሲሆን፣ ሰሞኑን ደግሞ የፌዴራል ፖሊሶችን ማስመረቁን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

በሁርሶ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ በድብቅ ለወራት ያህል ሲሰለጥኑ የነበሩ ከ2 ብርጌድ በላይ የፌዴራል ፖሊስ ምልምሎች ቅዳሜ ታህሳስ 26 ቀን 2000 ዓ.ም የተመረቁ ሲሆን፣ እነዚህ የፌዴራል ፖሊሰነት ስልጠና ወስደው የተመረቁት ፖሊሶች ላይምሰል ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ ቢሆንም 60 በመቶ ያህል ግን ከትግራይ ውስጥ የተመለመሉ መሆኑን የፌዴራል ፖሊስ ምንጮቻችን አጋለጡ::

በዘር ላይ የተመሰረተው የወያኔ በድን በድብቅ በሁርሶ ሲያሰለጥን የነበረውን በሰው ኃይልና በትጥቅ የተሟላውን 2 ብርጌድ የፌዴራል ፖሊስ ኃይል ቅዳሜ ታህሳስ 26 ቀን 2000 ዓ.ም እንዳስመረቀ ምሽቱን በ100 የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ በመጫን እሁድ አዲስ አበባ በየመስፈሪያ ካምፓቸው ያስገባቸው ሲሆን፣ ነባሮቹ የፌዴራል ፖሊሶች ከሕዝቡ ጋር ተላምደዋል በሚል ወደተለያዩ ከተሞች ተበታትነው እንዲመደቡ መደረጉን ምንጮቹ ገልፀዋል::

በጦር ኃይል የሚተማመነው ፀረ ዴሞክራሲ የሆነው የወያኔ ቡድን ባለበት ውጫዊና ውስጣዊ ፍርሀት የተነሳ በየጊዜው በየወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፑ ፖሊሶችንና ወታደሮቹን እያሰለጠነ ሀገሪቱን በወታደራዊ ብዛትና በፌዴራል ፖሊስ ኃይል ለመቆጣጠር እየጣረ ያለው የስልጣን ስግብግቡ ወያኔ ዛሬም በድብቅ የቴኩዋንዶ ስልጠና ሲሰጣቸው የነበሩ የፌዴራል ፖሊስ ወታደሮችን ማስማረቁ አስገራሚ እና ከሐገሪቱ ኢኮኖሚ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ኃይል እየገነባ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በአሁን ወቅት መላው የሀገሪቱ ሕዝብ በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ከመሆኑም ባሻገር የገጠሩ ሕዝብ በተለይ አርሶ አደሩ የግብር ክፍያውን በየጊዜው እየናረበት መጥቶ ዛሬ መክፈል ከሚችለው

በላይ እንደሆነበትና ቀየውን ጥሎ ለመሰደድ በዝግጅት ላይ መሆኑን የወያኔ ካድሬዎች ጠንቅቀው እያወቁ የማረጋጊያ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ በፌዴራል ፖሊሶች አማካኝነት እንደልቡ ረግጦ ለመግዛት ከመቼውም በላይ እየተዘጋጀ መሆኑ በጣም አሳፋሪና ከአንድ መንግስት ነኝ ከሚል ኃይል የማይጠበቅ ብልሹ አሰራር መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

የወያኔ ቡድን ባደራጀው የጦር ኃይል ብዛት ከአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው እንደሆነ የገለፁት ምንጮቹ በጦር መሳሪያ ግዥም ከፍተኛ ወጪ የሚያደርግ ለስልጣን እንጂ ለሕዝብ የማያስብ ስግብግብ ቡድን ነው ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በመሰሪ ባህርይው የሀገሪቷ ሕዝቦች ጠንቅቀው ያወቁት ቡድን መሆኑን የገለፁት ምንጮች የአለም ህብረተሰብ መንግስታትም ከመቼውም ጊዜ በላይ በኬንያ ምርጫ በተነሳው ረብሻ ደግሞ ያለውን ባህርይ ጠንቅቀው ሊረዱት እንደቻሉም ለማወቅ ተችሏል።

በቅርቡ በኬንያ የተካሄደውን የፕሬዝዳንታዊ ምርጫ አሸንፌያለሁ በማለት ፕሬዝዳት ሞያይ ኪባኪ ቢያውጅም የተቃዋሚ መሪው ግን የሕዝብ ድምፅ ተጭበራብሯል በማለት በየቦታው ሰልፍ በመጥራት ከፖሊሶች ጋር በተከሰተ ግጭት ከ500 በላይ ሰዎች የተገደሉ ሲሆን፣ የአለም መንግስታትና የአለም አቀፍ ድርጅቶች ምርጫው እንዲደገም ለሁለቱ ግለሰቦች ባቀረቡት ጥሪ ቢቀበሉም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ግን ውስጥ ውስጡን በመጓዝ ኪባኪ የድጋሚ ምርጫ ውስጥ እንዳይገባ በከፍተኛ ደረጃ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕዝብ ግንኙነት ቢሮ ምንጮቻችን አጋልጠዋል።

በአፍሪካ ሞዴል ተምሳሌት ይሆናል ተብሎ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የኬንያ ምርጫ የወያኔው ቡድን በገንዘብና በደህንነት ኃይል ለኪባኪ ድጋፍ በመስጠት ገና ከጅምሩ የምርጫውን ሂደት እንዲበላሽ ከማድረጉም በላይ ሁለቱ ቡድኖች በድርድር ወደ ድጋሚ ምርጫ እንዲሄዱ አለም አቀፍ መንግስታቶችና ድርጅቶች ግፊት በማድረግ ላይ ያሉ ቢሆንም የወያኔው መሪ መለስ ግን ይህ እንዳይሆን ከኪባኪ ጐን ተሰልፎ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ ከመሆኑም በላይ የተቃዋሚውን መሪ በስውር ለማሸመድመድ እየጣረ መሆኑን ምንጮቹ በዝርዝር ገልፀዋል።

በአፍሪካ ልዩ ነው የተባለለት የ1997 ዓ.ም የኢትዮጵያን ምርጫ አወናብዶ ከ200 በላይ ሰዎችን ገድሎ ስልጣኑን ለገዛ ራሱ ለመቆጣጠር የቻለ መሆኑና በዚህም በፈጠረው አፀያፊ ተግባር ውግዘት የደረሰበት ወያኔ በተመሳሳይ መልኩ የኬንያን ምርጫ ለዚህ ሁኔታ የዳረገው ኪባኪን አሳስቶ እንደሆነ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ክፍል የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀው በኪባኪና በተቃዋሚው መሪ እርቁ ተካሂዶ በሠላማዊ መንገድ እንዳይጠናቀቅ ለማድረግና «እኛ ብቻ አይደለንም ሁሉም አፍሪካዊ መንግስት በምርጫ ሳቢያ ሰው ይገድላል» ለማለት በርትቶ እየሰራ እና የአለም መንግስታት የጣሉበትን ማዕቀብና ፊታቸውን ያዞሩበትን ለመለመኛ እየተጠቀመበት መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል።

የወያኔው ቡድን በዜጎች ላይ ምርጫውን ተከትሎ ባደረሰው የዜጎች ፍጅትና መልካም አስተዳደር በሀገሪቷ እንዳይሰፍን፣ ተጠያቂነት እንዳይኖር፣ ዲሞክራሲ ፣ የፕሬስ ነፃነት፣ እና የመሳሰሉት እንዳይኖሩ በማድረጉ ሊያስተካክለውና ሊያርመው ይችላል በሚል ኤች 2003 ሕግ በአሜሪካ ምክር ቤት እንዲፀድቅ ያደረጉት ዶናልድ ፔይን በአስመራ የ3 ቀን ይፋ ጉብኝት በማድረጋቸው ብቻ ወያኔ ስማቸውን በማጥፋት ላይ መሆኑን የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ምንጮች ገለፁ::

ዶናልድ ፔይን ከሻዕቢያው ፕሬዝዳንት፣ ከኤርትራ የእምነት አባቶችና ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተወያዩ ተብሎ የተነገረውን ዘገባ የተከታተለው የወያኔ ቡድን ከመበሳጨቱ የተነሳ የሚይዘውና የሚጨብጠውን በማጣቱ አንድ የአሜሪካ ከፍተኛ ባለሥልጣንን እያብጠለጠለ በሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ ስማቸውን በማጥፋት ላይ መሆኑንም ገልፀዋል::

በተለይም የ1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ በወቅቱ ጦሩን የማዘው እኔ ነኝ በማለት የወያኔው መሪ ስልጣኑን በራሱ ኃይል የተቆጣጠረው በመሆኑና ዶናልድ ፔይን ካስቀመጡት ህጎች መካከል ዜጎችን የገደለና ያስገደለ በህግ እንዲጠየቅ በማለት የጠየቁ በመሆኑ ወዲ ዜናዊን ያናደደ ከመሆኑም በላይ ጨርቁን ጥሎ ለመሄድ እየዳዳው መሆኑን የገለፁት ምንጮች ይህ ንዴት ሳይበርድ ሰሞኑን ደግሞ ከሻዕቢያ ጋር በአስመራ መገናኘታቸው እጅግ ያበገነው ከመሆኑም በላይ ያሳረረው እንደሆነ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በሌላ በኩል የወያኔ ጦር በሞቃዲሾ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ ወድቆ ባለበት በዚህ ወቅት የአፍሪካ ህብረት ጦር ሶማሊያ እንዲገባ እነ መለስ ዜናዊ ቢወተውቱም እንዳሰቡት ሳይሳካላቸው መቅረቱና በየቀኑም የእስላማዊ ሕብረቱ ተዋጊዎች በሚሰነዝሩት ጥቃት ቢያንስ 6 እና ከዚያ በላይ ሟች ወታደሮች እንደሚገኙና በርካታ ቁስለኞችም በጦር ሂሊኮፕተር ወደ ሐረርና አዲስ አበባ እየተመላለሱ እንደሚገኙ የመላከያ ምንጮቻችን ገለፁ::

በሱማልያ የሽግግር መንግስቱን በእግሩ አቆማለሁ በማለት በየቀኑ የሀገሪቷን ዜጎች እያስጨረሰ ያለው ወያኔ እንዳሰበው ቀላል ሳይሆን ቀርቶ ዛሬ በአጣብቂኝ ውስጥ በሚገኝበት ወቅት በስልጣን ላይ ለማቆየት የሚሯሯጥላቸው አብዱላሂ የሱፍ በጠና ታምመው ሐሙስ ታህሳስ 24 ቀን ከባይደዋ አዲስ አበባ ምሽቱን ገብተው በጦር ኃይሎች ሆስፒታል ለ3 ቀናት ሕክምናቸውን ሲከታተሉ የነበረ ሲሆን፣ የጤንነታቸው ሁኔታ ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሰ በመሄዱ እሁድ እለት ወደ ለንደን እንደበረሩም የቤተ መንግስት ምንጮቻችን ገልፀዋል::

ወጪውን በሙሉ የወያኔ ቡድን የሚሸፍን ሲሆን፣ በአንፃሩ የሀገሪቷ ሕዝቦች የዕለት ጉርስ ተቸግረው ባለበት ወቅት ኢትዮጵያን ለወረረና በርካታ ዜጎችን ላሰቃየ የዚያድባሬ መኮንን ከፍተኛ ወጪ እያደረጉ ማሳከማቸውና ማንደላቀቃቸው የሚገርምና የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ በሀገር ሀብት በምንቸገረኝነት እየመዘበሩ ነው ሲሉም ምንጮቹ ገልፀዋል::